የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/664

ቀን ሐምሌ 7 ቀን 2014 ዓ.ም.

**ለብልጽግና ፓርቲ (ብልፅግና)**

**አዲስ አበባ፤**

መጋቢት 22 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ብፓ/ምፕዋፅኃ/1062/14 ለቦርዱ በተፃፈ ደብዳቤ ከመጋቢት 2- 4 ቀን 2014 ዓ.ም. ፓርቲ ያደረገውን የፓርቲው 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ በሚመለከት የጉባኤውን ሪፖርት ለቦርዱ ቀርቧል።

ቦርዱ ሚያዝያ 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ያቀረባቸውን የጠቅላላ ጉባኤ ሰነዶች እና ጠቅላላ ጉባኤውን በታዘቡት የቦርዱ ተወካዮች የቀረበውን ሪፖርት መርምሮ የጠቅላላ ጉባኤውን ሂደት፣ በጉባኤው የተላለፉ ውሳኔዎች እና የተደረጉ ምርጫዎችን በተመለከተ ውሣኔ ለመስጠት ተጨማሪ ሰነዶች እና መረጃዎችን ማየት በማስፈለጉ ፓርቲው ሰነዶቹን እንዲያቀርብ ሚያዝያ 19 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር አ1162/11/592 በተፃፈ ደብዳቤ ተገልፆለታል።

በዚሁ መሠረት ፓርቲው ሚያዝያ 21 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ብፓ/ምፕዋጽኃ/1194/14 በተፃፈ ደብዳቤ ተጨማሪ ሰነዶች ለቦርዱ አቅርቧል።

ሆኖም ቦርዱ የቀረበውን ሪፖርት እንደገና በመመርመር አሁንም ተሟልተው ያልቀረቡ ሰነዶችና መረጃዎች መኖራቸውን ተገንዝቧል። በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘረትን ሰነዶችና መረጃዎች እስከ ማክሰኞ ሐምሌ 12 ቀን 2014 ዓ.ም. ድረስ አሟልታችሁ እንድታቀርቡ ያሳውቃል። ይኸውም፡-

- የቀረበው የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባኤ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ በፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የተፈረመ ሳይሆን በአንድ ሰው ብቻ ተፈርሞ በመቅረቡ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ተፈርሞ እንዲቀርብ፣
- የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ መጋቢት 4 ቀን 2014 ዓ.ም. ያካሄደው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በሚል በፓርቲው የቀረበው በተሳታፊ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በየገጹ ያልተፈረመ በመሆኑ በአባላቱ ተፈርሞ እንዲቀርብ፤

ለድምጽዎ የሚያምኑን



ፌስቡክ /national-electoal-board-of-ethiopia-nebe
ትዊተር @NEBEthiopia
ኢሜይል contact@nebe.org.et
ድረ-ገጽ www.nebe.org.et

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚገን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
ስልክ +251 115 153468
ፋክስ +251 115 510025

- የፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴው በ17/06/2014 ያካሄደው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በሚል የቀረበው ሰነድ በሚል የቀረበው ሰነድ በእያንዳንዱ ገፅ በማዕከላዊ ኮሚቴው አባላት ያልተፈረመ በመሆኑ ተፈርሞ እንዲቀርብ፣

- የቀረበው የፓርቲው ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በ20/06/2014 ዓ.ም. ያካሄደው ስብሰባ ቃለ ጉባኤ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት በእያንዳንዱ ገፅ ያልተፈረመ በመሆኑ ተፈርሞ እንዲቀርብ፤

- ከፓርቲው ሊቀመንበር እና 2ቱ ምክትል ሊቀመናብርት በተጨማሪ በጠቅላላ ጉባኤው የተመረጡ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ብዛት 222 ነው። ይሁንና በጠቅላላ ጉባኤው ቃለ ጉባኤ ያሸነፉ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት በሚል የቀረበው የ208ቱ ዝርዝር ብቻ በመሆኑ ሁሉም የተመረጡት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ዝርዝር ተሟልቶ እንዲቀርብ ቦርዱ ያሳውቃል።

ከበጎ ምኞት ጋር

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ